# ምነዋ በኢሕአፓ

(ይድረስ ለጭፍን ጸረ-ኢሕአፓዎች)

እናት ሃገርን ያህል-
ታላቋን ምሰሶ ማገር
የኛነታችን መለያ-
ዞሮ መግቢያችንን በር
አካሏን ቆርሶ የሰጠ-
ታሪኳን ያጎደፈ
ሕጻን አዛውንት ሳይመርጥ-
በጅምላ የቀጠፈ
እያሰረ እያንገላታ-
እያመቀ እየረሸነ
ወገንን በዘር በሐይማኖት-
እየለያየ እየበተነ
ትውልድን እየመተረ-
ሃገር እያመከነ
ጸረ-ኢትዮጵያው ሕወሃት-
ታላቁ ጭራቅ ተቀምጠ
ጦርነት ጫሪው ጸረ-ሰላም
ዓይኑን አጉርጦ አፍጦ
በሕዝብ ደም እየታጠበ-
የሃገር አደራ እየበላ
ምነዋ በኢሕአፓ-
የፈጠራ ውንጀላ?
ምነዋ በኢትዮጵያዊው-
በኢሕአፓ በፋና ወጊው?
የፈጠራው ክስ ተሰፋፋ
ውግዘቱ በረከተ
ለሕዝብ ስለደማ
ስለቆሰለ ስለሞተ?
ምነዋ?

የፖለቲካ ሀሁ-
አቡጊዳ አስቆጥሮ
ክቡር ሕይወትን ያህል-
መስዋዕትነት ከፍሎ
በገንጣይ አስገንጣዮች
በጎሰኞች ላይ ዘምቶ
ሰራዊት ክተት ብሎ-
ጀግንነትን በአርአያነት
ምሳሌ ሆኖ በኖረ-
እየታገለ በጽናት

ምነዋ የወሬ አርበኛው-
በኢሕአፓ ላይ በረከተ
ወገን በወገኑ ላይ
ምነዋ ጦር ከተተ?

አይበጅም ነበረ ከቶ
በሃገርና በሕዝብ ጠላት
ተባብሮና ተስማምቶ
ትግልን በሕብረት መምራት
የጋራ ጠላት እስኪወድቅ
ሕዝብ ፍርዱን እስኪሰጥ
ሁሉም የጁን አግኝቶ
ታሪክ ተዘክሮ ሲቀመጥ
አይደርስም መቧጨቁ
ሕዝብና ሃገር ሲደላደል
ሁላችንም ተመዝነን
ሲታወቅ ከባድ ከቀላል?
እርስ በርስ በመካሰስ
ሃገርና ሕዝብ ላይድን
ለጠላት እየተመቹ
የሱን ክንድ ማደንደን
መቼ ነው የሚበቃ
በሃሰት መወነጃጀል
ጥላሸት መቀባባት
አንዱ በሌላው መንጠልጠል።

የኢንተርኔቱ አርበኛ
የድረ ገጹ ፋኖ
ኢሕአፓን በመወንጀል
ስምህ ሊወጣ ገንኖ
መስሎህ እንደሆን ቂለሃል
እራስህን አታለሃል
እውነትና ንጋት እንደሁ
እያደር መጥራቱ ላይቀር
በፈጠራ ወሬና
በአሉባልታ ጥጋብ አትሰከር።
ኢሕአፓ እንደሁ ከትግሉ
ፍንክች ላይል ላይቀለስ
ይልቅ ጊዜህን አታጥፋ
ወደሕዝብ ትግል ተመለስ።

የሃገርህ ጥሪና
የወገን ዋይታ ለቅሶ
እርስ በርስ በመጠፋፋት

ላይወገድ ጨርሶ
እሽኮለሌ እየወጣን
ጠላት በኛ ከሚስቅ
ቆፍጠን ጀገን እንበል
ገበናችንን እንደብቅ።
ኢትዮጵያና ተተኪ ትውልድ
ዘላለማዊነታቸው ላይቀር
የወገን ሰቆቃ አቁመን
እንሙት እንቀበር።
ታሪክ ሰርቶ ማለፍና
አርአያ መሆን ለትውልድ
ህውልት ማቆም ነው ለራስ
ለወገን ለዘመድ አዝማድ።

ይልቅ ራሳችንን እናሙኝ...
ለጠላት ተመቻችተን አንገኝ።
ላለፈ ጥፋት እንደሁ
ሁላችን ነን ተጠያቂ
ከመካከላችን አንድም የለም
እንደ ጲላጦስ እጁን ታጣቢ።
በሆነውም ባልሆነውም
በረባውም ባልረባውም
ኢሕአፓን በመወንጀል
ሃገርና ሕዝብ አይድንም።
" የጦር ወታደር አሽዋ አበላ
መንግስቱን መደገፍ ትቶ
ለዚያድ ባሬ አደላ
መሪዎቹ እየሸሹ አባላቱን አስጨረሱ
በብሄር ብሄረሰብ ፍላስማ
ገንጣዮችን አነገሱ..."
ወዘተ... ወዘተ... እያሉ
በኢሕአፓ ቢያነጣጥሩ
ተቃራኒው ለመፈጸሙ
ታሪክ ነው ምስክሩ።
ይልቅ...
ኢሕአፓን በጥላሸት
ማስማመሩን ትተን
ከራሳችንና ከእውነት ጋር
ለሃቅ በሃቅ ተጋብተን
ለጋራዋ ሃገራችን
ለምስኪኑ ሕዝባችን
ምህላ እንግባ ለመጣል
የጋራ ጠላታችንን።

ለምን በብርቱ አይቆጨን?
ለምንስ አይሰቀጥጠን?
አለፉኮ ሁለት አሰርታት
እርስ በርስ ስንባላ
አንዳችን አንዳችንን
ቀርጥፈን ልንበላ
ጉሮሮ ለጉሮሮ
መያያዝ እስኪቀረን
ተጠፋፋን ተሻኮትን
ባይተዋር እስኪታዘበን።
ሃገራችን ተገንጥላ
መልኳ እኮ ተቀየረ
ባንዲራችን ምልክታችን
ከተራ ጨርቅ ተቆጠረ
ያገር አንድነት ቀደምቶች
በነፍጠኝነት ተኮነኑ
ኢትዮጵያውያን ነን ለማለት
የሚጠየፉ በቀሉ
ሕዝበ ውሳኔ ተሸሮ
ፍርደ ወያኔ ነገሰ
የሕዝብ ልጆች ተመራጮች
ወደ ወህኒ ተነዱ
ለጀሮ እስኪቀፍ ድረስ
ወገኖቻችን ታረዱ::
አፈ-ሕዝብ ጋዜጠኞች
መምሕራን የዕውቀት አባቶች
ልሳናቸው እንዲዘጋ
አጎብድደው እንዲኖሩ
በእኔን ያያህ ተቀጣ
ሞቱ ተጋዙ ታሰሩ።

እንዲህ ጥቂቶች በብዙሃን ላይ
የግፍ ዝናብ ሲያዘንቡ
ጎሰኞችና ጠባቦች
የድል ከበሮ ሲደልቁ
ያሳደዱን ያሰሩን
ለግዞት ያበቁን አነሰና
በጦርነት እሳት ሊማግዱን
ሲገበዙ እንደገና
የኛ እርስ በርስ መተላለቅ
በፈጠራ ወሬ መድመቅ
ምን ይሉት ዘመን ይሆን
ይህ የደረስንበቱ?
በራስ ላይ የሚስቅ ጥርስ

የተፈጠረበቱ።
ከቶ ምን ትውልድ ነን
ለጠላት የምንመች
ገዳያችንን ትተን
በወዳጃችን የምንዘምት?
መቼ ይሆን የምንነቃ
በዋናው ጠላት የምናተኩር?
የአዋጁን ባዋጅ አድርገን
ሚስጥራችንን ምንቋጥር?
መቼ ይሆን ለታላቋ
ለእናት ሃገራችን አንድነት
በጋራ በትብብር
የምንታገል በሕብረት?

እርግጥ ነው
ሂስ ያሳድጋል
በጎውን ያሞግሳል
ከጥፋትም ያርማል
ግና የሂስ ዓላማው
ጥፋት ፍለጋ ከሆነ
ሂስ ለመስጠትና መቀበል
ቅን ልቡና ከሌለ
ማን ለምን እንደሚሄስ
አስቀድሞ ካልታወቀ
ፍርደ-ገምድልነት ነው
ሂስ በቅጡ ካልታሰበ።

እናም መተራረሙ
መተቻቸቱ ሳይከፋ
ከቆሙለት መተክል
ከዓላማ የሚገፋ
ለመጨራረስ እንዳይሆን
ለጠላት የሚጠቅም
ሃይላችንን የሚበትን
አንድነትን የሚያጨልም
ጊዜ እናጥፋ በከንቱ
የቁራ ጯሂ እንሁን
ይልቅ በመተቃቀፍ
ላገር አለኝታ እንሁን።

እናም...

ኢሕአፓን በጥላሸት
ማስማመሩን ትተን

ከራሳችንና ከእውነት ጋር
ለሃቅ በሃቅ ተጋብተን
ለጋራዋ ሃገራችን
ለምስኪኑ ሕዝባችን
ምህላ እንግባ ለመጣል
የጋራ ጠላታችንን!
ምህላ እንግባ ለመጣል
የጋራ ጠላታችንን!!
ምህላ እንግባ ለመጣል
የጋራ ጠላታችንን!!!

በብሌን ዓለም አየሁ
ኦገስት 2006